# የመጽሀፍ ግምገማ

ሲሳይ መንገስቴ አዲሱ (ከኦስትሪያ፣ ግራዝ)

ሚያዚያ 24/2009 ዓ.ም

**የመጽሀፉ ርዕስ፡** ያልተዘመረላቸው፡ የኢህዴን/ብአዴን እንስት ታጋዮች የትግልና የድል ታሪክ

**የመጽሀፉ ደራሲ፡** ታጋይ ገነት ታደሰ (የኢህዴን መስራችና በአሁኑ ወቅት የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባል)

**የገጽ ብዛት፡** ፎቶግራፎችንና የዋቢ ጽሁፎችን ዝርዝር ጨምሮ 152

**መግቢያ**

የድሮዋ የኢህአፓና ኢህዴን ታጋይ የአሁኗ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባል ክብርት ወ/ሮ ገነት ታደሰ ከኢህዴን/ብአዴን መስራች ሁለት ሴቶች መካከል አንዷ በመሆኗና እድል ቀንቷት እስካሁንም ድረስ በህይወት መቆየት በመቻሏ የመስወአትነቷን ፍሬ ለመቋደስ በቅታለችና በዚህ አጋጣሚ እንኳን ደስ አለሽ ማለት አፈልጋለሁ፡፡ በዛ ፈታኝና እልህ አስጨራሽ ወቅት እሷን ጨምሮ አብረዋት የተዋደቁትን ሴት ታጋዮች ፖሊቲካዊና ወታደራዊ ሚና እንዲህ በመጽሀፍ መልክ ሰንዳ በማሳተም ሙሉ ነው ባይባለም ታሪካዊ ገድላቸውን በዝርዝር ፈትሻ ልታሳየን መፈለጓ በራሱ እጅግ የዘገየ ቢሆንም በእጅጉ የሚያበረታታ ስራ ሆኖ ስላገኘሁት በድጋሜ እንኳን ለዚህ አበቃሽ ለማለት እወዳለሁ፡፡

በተለይም ኢህዴን/ብአዴን በትጥቅ ትግሉ ወቅት ያበረከተው ወታደራዊና ፖሊቲካዊ አስተዋጽኦ በተለያዩ ምክንያቶች ተደፍቆ በመቆየቱ ምክንያት እስካሁን ድረስ ያን የያህል ጎልቶ እንዳይወጣና መላው የኢትዮጵያ ህዝብም በአግባቡ እንዳያውቀው እየተደረገ በነበረበት ይልቁንም በተቃራኒው ኢህዴን/ብአዴን እንደ ድርጅት እና መሪዎቹ እንደ ግለሰብ የህወሀት ተላላኪ ተደርገው እንዲታዩ ማድረግ የሚያስችሉ ስራዎች በአንዱ ወይም በሌላኛው ወገን እየተሰሩ ባሉበት በአሁኑ ወቅት ታጋይ ገነት ይህን መጽሀፍ በማዘጋጀት አሳትማ ለተደራሲያን እንዲቀርብ ማድረጓ በአዎንታ መታየት አለበት ብየ አምናለሁ፡፡

በመሆኑም በዚህ መጽሀፍ አማካኝነት በትጥቅ ትግሉ ወቅት የሴቶች ተሳትፎ እስከምን ድረስ የዘለቀ እንደነበር ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርሁት ያን ያህል የተሟላ ነው ሊባል የሚችል ባይሆም በዝርዝር ለመዳሰስ ጥረት አድርጋለች ባይ ነኝ፣ በአጠቃላይ ሲታይም መልካም ነገሩ ይጎላ ካልሆነ በስተቀር መሰረታዊ ነው ሊባል የሚችል የታሪክ ዝንፈትም

ሆነ መፋለስ የሌለበት ስራ እንደሆነ ማስቀመት ይቻላል፡፡ እንዲውም የኢህደን ታሪክ ተብሎ ከተጻፈው የድርጅቱ ታሪክ በተሻለ ታሪክ ነጋሪ ስራ ነው ሊባልም ይችላል፡፡ ይህም ሆኖ ስራዋ ምንም አይነት እንከን የለውም ብሎ ለመመስከር የማያስችሉ ጉድለቶች እንዳሉበትም ይታመናል፣ ቀጥሎ ባሉት አንቀጾች ላይ በዝርዝር ለማሳየት የምሞክረውም መጽሀፉ ውስጥ የተስተዋሉትን ጉድለቶችና መደረግ የነበረባቸውን ሁኔታዎች ይሆናል፡፡

## አቀራረብና ሚዛናዊነትን በተመለከተ

በመጽሀፉ ውስጥ ከተስተዋሉት ውስንነቶች መካከል በቀዳሚነት ሊጠቀስ የሚችለው ከአደረጃጀት ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችለው ጉድለት ነው፣ መጽሀፉ በዋናነት በሁለት ክፍሎችና በበርካታ ምዕራፎች ተከፋፍሎ መዋቀር ሲገባው ሁሉንም በክፍል በክፍል አደራጅቶ ማቅረቡ የክፍልንና የምዕራፍ ክፍፍሎችን አስፈላጊነትና ዋጋ ትርጉም የለሽ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ በክፍል መልክ ሊገለጹ የማይገባቸው ስራዎች በአንድ ክፍል ስር ተካተው መቅረባቸው ተገቢ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ በዚህ ረገድ በምሳሌነት ሊገለጽ የሚችለው ከክፍል አንድ እስከ ክፍል አምስት ድረስ የሚገኙት የመጽሀፉ አደረጃጀቶች በአንድ ክፍል ስር ሆነው በተለያዩ ምዕራፎች መከፋፈል ነበረባቸው፣ ክፍል ስድስትና ክፍለ ሰባት ደግሞ በአንድ ክፍል ተጠቃለው በክፍል ሁለት ስር የተለያዩ ምዕራፎች ሆነው መደራጀት ይችሉ ነበር፡፡

ሌላው በጉድለትነት ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ደግሞ ታጋይ ገነት ስለራሷ ስትገልጽ የቃላት አጠቃቀሟም ሆነ እውነትን በትክክል የመግለጽ ሀይሏ እየደከመና እጅግ ቁጥብነት እየተንጸባረቀበት መጥቶ እንደነገሩ የሆነበት ሁኔታ ይታያል (ከገጽ 25-50)፣ ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ በሚባልበትና ትንሽ ነገር ሰርቶ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ አድርገው በየድረ-ገጹም ሆነ መደበኛ የመገናኛ ብዙሀንን ጨምሮ በተገኘው መድረክ ሁሉ የራሳቸውን ሚና ከፍ አድርገው የሚገልጹ ወገኖች በየቦታው በፈሉበት በዚህ ዘመን ወ/ሮ ገነት ታደሰ በይሉኝታ ተሸብባ ይመስላል ቢያንስ የዋለችበትን የጦር ሜዳ ውሎ፣ በየአውደ ውጊያ የነበራትን የአዋጊነት ሚናና የአካባቢው ህዝብና አብረዋት ተሰልፈው የተዋደቁ ታጋዮች በግልጽ ያሳዩዋት የነበረውን አድናቆት እንኳ በአግባቡ መግለጽ አልቻለችም፡፡

እኔ ራሴ ወደ ትግል ሜዳ ከመግባቴ በፊትም ሆነ ወደ ትግሉ ተቀላቅየ እንቀሳቀስ በነበረበት ወቅት ስለ ታጋይ ገነት እሰማው የነበረው ገድል በዚህ መጽሀፍ ውስጥ በእጅጉ

ኮሶ እንዲታይ አድርጋዋለች፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ስለእሷ ይነገር የነበረው ነገር ያን ያህል ተጋኖና ከእውነታውም የራቀ ሆኖ ሳይሆን ራስን በአግባቡ ያለመግለጽ ባህላችን ተጭኗት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ከ1970ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ እንስከ 1970ዎቹ መጨረሻ ድረስ በነበሩት አመታት በሰራዊቱ ውስጥ አመራር ሆና በላስታና ዋግ አውራዎች ውስጥ በተንቀሳቀሰችባቸው ወቅቶች የገነት ጦር መጣ ከተባለ የደርግ ነጭ ለባሾች መግቢያ ቀዳዳ አጥተው በእጅጉ ይርበደበዱ እንደነበረ ተደጋገሞ የተባለ ጉዳይ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

የዚህን ታሪካዊ ክስተት እውነትነት ለማጠናከር የኢህዴን-ብአዴን ነባር ታጋይ የሆነው ብርጋዴር ጀነራል አከለ አሳየ በትጥቅ ትግሉ ወቅት የኢህዴን ሰራዊት የነበረውን ወታደራዊ ሚና ለማሳየት በማሰብ በጻፈውና ቁጥር 2 ብሎ ባሳተመው መጽሀፉ ገጽ 276-277 ላይ ስለ ታጋይ ገነት ያሰፈረውን ሀሳብ እንዳለ በመውሰድ ከገጽ 54-55 ለማካተት መሞከሯ አንድ ነገር ሆኖ የዚህም ሀሳብ ቦታ ከአጠቃላዩ የሴት ታጋዮች ክፍል ወጥቶ በገነት የተናጠል ታሪክ ውስጥ መካተት እንደነበረበት ይታመናል፡፡ ሆኖም ለአጠቃላዩ የሴቶች ትግል ማሳሳ መሆን የሚችል ሆነ ከተገኘ በድጋሜ መግለጽ ይቻል እንደነበር ሳይዘነጋ ማለቴ ነው፡፡

የዚህ አይነቱን ችግር ለማስወገድ ይረዳ ዘንድም የታጋይ ገነትን የትግል ታሪክ በቅርብ የሚያውቃትና ለረዥም ገጊዜ አብሯት የታገለ አሊያም ከራሷ አንደበት ብቻ ሳይሆን ከሌሎች መስራችና ነባር ታጋዮች እንዲሁም ከላስታና ዋግ አውራጃዎች ስለእሷ ምስክርነት የሚሰጡ ሰዎችን በማነጋገር ሌላ ሰው እንዲጽፈው ተደርጎ የዚህ መጽሀፍ አካል ለማድረግ በቢሞከር ኖሮ ምንኛ መልካም በሆነ ነበር፡፡ ምናልባት ትክክለኛዋን ገነት በሚገባ የማየት እድል እናገኝ ነበር የሚል ጽኑ እምነት አለኝ፣ ለምሳሌ ከኢህዴን መስራች ሴቶች ውስጥ አንዷ የሆነችውን የታጋይ አሰፋሽ ጣሰውን የትምህርትና የትግል ታሪክ በአጭሩም ቢሆን በሚገባ ስላቀናበረችው ስለ ታጋይ አሰፋሽ ሙሉ ስዕል ሊሰጥ በሚችል መልኩ ተገልጧል፡፡

ሌላው በታጋይ ገነት ሚናና ተሳትፎ ውስጥ መገለጽ የነበረበት በአንድ ወቅት የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሆና ማገልገሏና የኢህአዴግ ምክር ቤት ጽ/ቤት ሀላፊ በመሆንም ጭምር መሰራቷ እንደ አንድ የታሪኳ አካል ሆኖ መታየት ስላለበት እንደ ዋዛ መዘለል አልነበረበትም ወይም ሳይታወስ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ ነበር፡፡ እንዲሁም ከስም አጠራር ጋር ተያይዞ መለስተኛ ስህተቶችም ተስተውለዋል፣ ለምሳሌ ማርታ መብርሀቱን ማርታ መብራቱ (ገጽ 3) እና ሲሳይ ንጉሱን ሲሳይ ንጉሴ (ገጽ 7) የሚሉት ግድፈቶች

በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሱ ሲሆኑ የቦታ ስም ላይም ተመሳሳይ ስህተት ተፈጽሞ ተመልክቻለሁ፣ ለምሳሌ ራያ ውስጥ ኩኩፍቱ በመባል የሚታወቀውን አካባቢ ጉጉፍቱ (ገጽ 41) በማለት ስለጠቀሰችው በተወሰነም ቢሆን አንባቢያንን ግራ ሊያጋባ ወይም ሊያደናግር መቻሉ አይቀርም፡፡ ሌላው በአጋጣሚ ወይም በስራ ምክንያት ያገኘቻቸውን ታጋዮች ስም በትክክል ጠቅሳ ስታበቃ ለአንዳንዶቹ የተወሰነ ማብራሪያ ጭምር እየሰጠች ያለፈች ቢሆንም (ለምሳሌ ወ/ሮ ዘነቡ ታደሰን ኢህአሠ ውስጥ በነበረችበት ወቅት እና አቶ ልጃለም ወልዴን ኢህዴን ከተመሰረተ በኋላ)፡፡

ይሁን እንጂ የቀድሞ ባለቤቷን ማለትም ኡስማን አሸኔ የተቀበረበትን ቦታ ለማየት ወልዲያ ከተማ በሄደችበት ወቅት በጊዜው የኢህዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና የወልዲያ ሪጅን ሀላፊ የነበረውን ታጋይ ይርጋ አበበን በቅጽል ስሙ ሀው ጃኖን አግኝቸው ነበር በማለት ብቻ ማለፏ ተገቢ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ሀው ጃኖ ማለት በትግርኛ ቋንቋ የጃኖ ወንድም ማለት ሲሆን ይርጋ አበበ ታጋይ ገነት አሳምራ እንደምታውቀው በጦር ሜዳ ውሎ ላይም ሀው ጃኖ እያለ በመፈከር በግንባር ቀደምነት እየተዋጋ ያዋጋ ስለነበርና በዚህም ምክንያት በኢህዴን ታጋዮች ዘንድ ጀብደኛ እየተባለ ይገመገም እንደነበርም ታጋይ ገነት ከእኔ በተሻለ አሳምራ እንደምታውቀው ምንም አይነት ጥርጣሬ የለኝም፡፡

በጦር ሜዳ ውሎው ይርጋ አበበ ሀው ጃኖ የሚለውንና በሚወዳት እህቱ ስም የሚያሰማውን መፈክር ደጋግመው የሰሙ ታጋዮች ሀው ጃኖ እያሉ በመጥራታቸው ምክንያት የራያው አንበሳ ይርጋ አበበ በብዙዎቹ የኢህዴን ነባር ታጋዮች ዘንድ በዚህ ቅጽል ስሙ ይበልጥ እየታወቀ መምጣቱ ይተታወቃል፡፡ ሆኖም ታጋይ ገነት የዚህን ጀግና ታጋይ ትክክለኛ ስም አንስታ የተወሰነም ቢሆን ማንነቱንና በትግሉ ውስጥ የነበረውን ሚና ለማስታወስ የሚያስችል መረጃ ወይም እውቀት ሳይኖራት ቀርቶ ሳይሆን ወደ ኋላ ላይ የተለየ ሀሳብ ይዞ መገኘቱና በዚሁ የተለየ ሀሳቡ ሳቢያ ለራሱም ሆነ ለንጉሴ ጂሞ ህይወት መጥፋት ምክንያት በመሆኑ ትክክለኛ ስሙንና ተግባሩን አንስታ በትንሹም ቢሆን ስለእሱ እንዳትገልጽ ያደረጋት ይመስለኛል፡፡

በሌላ አገላለጽ የዚህን ጀግና ታጋይና መሪ ትክክለኛ ስም ጠቅሳ ገድሉንም ዘርዘር አድርጋ መግለጽ ያልፈለገችው ምናልባትም በ1983 ዓ.ም አጋማሽ ላይ በኢህአዴግ ውስጥ የህወሀት የበላይነት በግልጽ እየተንጸባረቀ ነው፣ የኢህዴን አመራርም ይህን ሁኔታ እስከመቼ ነው በዝምታ እየተመከተ ማለፍ የሚኖርበት? የሚል ጠንከር ያለና በጽሁፍ መልክ ጭምር

ሀሳቡን በማዘጋጀት የተለየ አቋም ይዞ ከአቶ መለስ ዜናዊና ታምራት ላይኔ ጋር ጭምር በድፍረት በመሟገቱ ምክንያት ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነቱ እንዲታገድ የተደረገበትና የኋላ ኋላ ደግሞ እንዲታሰር የኢህዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ በመወሰኑ ምክንያት የይታሰር ውሳኔውን ለማስፈጸም ከሄዱት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት መካከል ምን ጊዜም ቢሆን በተጠንቀቅ ላይ የነበረውና ከእጁ የማይለይ በነበረው ሽጉጡ ንጉሴ ጂሞን ገድሎ በእሱና አብሮት በነበረው የትግል አጋሩ ተይዞ የነበረውን የድርጅት ሰነድ ክብሪት ለኩሶ ሲያቃጥል እሱም በታጋዮች ጥይት አዲስ ዘመን ከተማ ላይ መገደሉ እንደ ብዙዎቹ የኢህዴን-ብአዴን ነባርና ከፍተኛ አመራሮች ምቾት አልሰጣት ብሎ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

ከዚህም ባሻገር ከኢህዴን መስረታ ጀምሮ በአመራርነትና ኋላ ላይ ደግሞ በሊቀመንበርነት ስላገለገለው ታምራት ላይኔ ምንም ነገር ሳትል ማለፏም ተመሳሳይ የሆነ ትዝብት ውስጥ እንድትገባ የሚያደርጋት ይመስለኛል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ በመጽሀፉ ውስጥ ቀላል የማይባል የአርትኦት ችግሮች ስላለበትም በተነባቢነቱ ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር እንደሆነ ይታመናል፣ ሌላው ጉዳይ መጽሀፉ በበርካታ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ መታተሙ እየታወቀና ይዘቱም ቢሆን ከ140 ገጽ ያልበለጠ ሆኖ ሳለ በ100 ብር ሂሳብ እንዲሸጥ መደረጉ እንኳንስ ዘንቦብሽ እንዷውም ጤዛ ነሽ እንደሚባለው ብዙሀኑ ተደራሲያን እጅ እንዳይገባ ምክንያት የሆነ ይመስለኛል፡፡

ይህም ሁኔታ ከአምስት አመት በፊት አቶ በረከት ስምኦን የሁለት ምርጫዎች ወግ በሚል ርዕስ ጽፈው ያሳተሙትን መጽሀፍ በ90 ብር ሂሳብ ገበያ ላይ በማቅረባቸው ሳቢያ ለምን እንዲህ ከፍ ባለ ዋጋ እንዲሸጥ አደረጉ ተብለው ሲጠየቁ በሸህ ሙሀመድ አሊ አላሙዲን ወጭ መታተሙን ረስተውት ይሁን በሌላ ምክንያት አይታወቅም ሁላችሁም እንደምታውቁት የወረቀትና የህትመት ዋጋ ውድ ስለሆነ ነው በዚህ ዋጋ እንድንሸጥ ያደረገን በማለት ትዝብት ውስጥ ያስገባቸውን መልስ መስጠታቸው ይታወሳል፡፡

በተረፈ ስለ ኡስማን አሽኔ (የቀድሞ ባለቤቷና የትግል አጋሯ) የትግል ታሪክ ለመጻፍ አስቤያለሁ በማለት በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ቃል መግባቷ እኔን ጨምሮ ለኢህዴን ነባር ታጋዮች በእጅጉ እንደሚያስደስተን በእርግጠኛነት መናገር ይቻላል፡፡ ታጋይ ኡስማን በመኪና አደጋ ወልዲያ ከተማ ውስጥ ሲሞት እኔ በክፍለ ህዝብነት ራያ-አላማጣ ወረዳ ውስጥ እሰራ ስለነበር የሞቱን ዜና አብረውን ከነበሩ ታጋዮች ጋር ሆነን ስንሰማ በእጅጉ ማዘናችንን አስታውሳለሁ፡፡ ታጋይ ኡስማን አሽኔ በጀግንነቱና በአመራር ብቃት በወቅቱ

ኢ.ህዴን ውስጥ ከነበሩት ፖለቲካዊና ወታደራዊ አመራሮች መካከል በግንባር ቀደምነት የሚጠቀስ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ደግነቱ ታጋይ ገነት እንዳለችው በመጨረሻዋ ስአትም ቢሆን ለስሙ መጠሪያ የሚሆነውን ማህደር ጌጡን ትቶልን አልፏልና እሱን ስናይ በእጅጉ እንድንጽናና ያደርገናል፡፡ የሚገርመው ታጋይ ኡስማን አሸኔ የኢ.ህዴን መስራችና ከፍተኛ አመራር በመሆን ለረዥም ጊዜ ያገለገለና በጀግንነቱም ስመጥር ሆኖ ሳለ እስካሁን ድረስ በስሙ የሚጠራ አንድ ነገር እንኳ አለመኖሩ የኢ.ህዴን-ብአዴን አመራርን ሊያስወቅሰው የሚገባ ጉዳይ ይመስለኛል፡፡

በመጨረሻም በመጽሀፉ ጀርባ ላይ አሁን ባለበት መልኩ ከመጽሀፉ የተወሰደ ሀሳብ ብቻ ከማስፈር ይልቅ ከኢ.ህዴን መስራች አባላት መካከል የተወሰኑት ስለ ታጋይ ገነት ታደሰ ጽናትና አጠቃላይ ባህሪ ምስክርነታቸውን ቢሰጡበት ወይም ረቂቁን የማንበብ እድሉ የነበራቸው ሰዎች የፈጠረባቸውን ስሜት ለተደራሲያን የሚያካፍሉበትና እግረመንገዱንም ተደራሲያን ይህን መጽሀፍ ቢያነቡት አንዳች ትምህርት ሊያገኙበት እንደሚችሉ የሚጋብዙበት ቢሆን ይመረጥ እንደ ነበር መግለጽ እወዳለሁ፡፡

ተጠቃሎ ሲታይ የታጋይ ገነት ስራ እንደ መልካም ጅምር የሚወሰድ ሌሎችም በውስጣቸው ታምቆ የሚንተከተከውን የታሪክ ማዕበል ከማርጀታቸው ወይም ይዘውት ወደማይቀረው አለም ከመሄዳቸው በፊት በታሪክነት ሰንደው እንዲያስተላልፉ ሊያበረታታ ይችላልና ለዚህ መልካም ስራዋ በድጋሚ ልትመሰገን ይገባል እላለሁ፡፡